# መዘጋጀት በረከቶችን ያመጣል

ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

ወንድሞች፣ በዚህ በሶልት ሌክ በጉባኤ አዳራሽ ውስጥ ያላችሁ በመመልከት የምታነሳሱ ናችሁ። በሳተላይት መተላለፊያ እንደእናንተ አይነት የክህነት ስልጣን ያላቸው ሌሎች ብዙ ሺህ ቤተክርስትያናት ውስጥ ተሰብስበው እንደሆነ ማወቁ ያስደንቃል። ዘጌነታችሁ ይለያያል፣ እና ቋንቋዎቻችሁም ብዙ ናቸው፣ ነገር ግን የሚያስተሳስረን አንድ ነገር አለ። የክህነት ስልጣንን እንድንሸከም እና በእግዚአብሔር ስም እንድንሰራ እምነት ተሰጥቶናል። የቅዱስ ታማኝነት ተቀባዮች ነን። ብዙም ይጠበቅብናል።

የክህነት ስልጣን ስብሰባን ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፍኩበት የማስታውሰው በዲያቆንነት ከተሾምኩ በኋላ፣ "Come All Ye Sons of God Who Have Received the Priesthood." የሚለውን ስንዘምር ነው። በዚህ ምሽት የዚያን ልዩ መዝሙር መንፈስ እንደገና በመድገውም፣ የክህነት ስልጣን የተቀበላችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ኑ፣ ጥሪያችንን እናስብባቸው፣ ስለሀላፊነታችንም እናሰላስላቸው፣ እና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንከተል እላችኋለሁ።

ከ20 አመት በፊት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስትያን አባል ነኝ የሚለውን መልእክት ከሚያቀርቡ ልጆች ጋር በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ላይ ነበርኩኝ። እነዚህ ልጆች ጌታን እና ሌሎችን ለማገልገል እንደሚሰለጠኑ አሳይተው ነበር። ሙዚቃው አስደሳች ነበር፣ እነርሱም መልእታቸውን በደንብ ነበር ያቀረቡት፣ ሰማይም መንፈስን ልኮ ነበር። አንዱ የ11 አምት የልጅ ልጄ የፕሮግራሙን ክፍሉን ሲያቀርብ ስለ መጀመሪያው ራዕይ ተናግሮ ነበር።፡ ከዛም በኋላ ወደ ወላጆቹ እና አያቶቹ ሲመጣ "ቶሚ ወደሚስዮን ለመሄድ እየደረስክ ነህ" አልኩት።

እርሱም "ገና ነኝ፣ ብዙ የምማረው ይቀረኛል" አለኝ።

በሚቀጥሉትም አመቶች በወላጆቹ እና በቤተክርስትያን አስተማሪዎቹና አማካሪዎቹ ምክንያት ቶሚ ተማረ። እድሜው ሲደርስም በሚስዮን እንዲያገለግል ተጠራ። ይህንንም በክብር ፈጸመ።

ወጣቶች፣ በሚስዮን ለማገልገል እንድትዘጋጁ እመክራችኋለሁ። ሊጠቅሟችሁ የሚችሉትን ትምህርቶች እንድትማሩ እና ብዉ ለመሆን መኖር የሚኖርባችሁን ህይወት እንድትኖሩ የሚረዷችሁ ብዙ መሳሪያዎች አሉ። እንደዚህ አይነት አንድ መሳሪያም በቀዳሚ አመራር እና በአስራ ሑለት ሐዋሪያት አመራር በኩል የታተመው *For the Strength of Youth* ነው።ይህም ከቤተክርስትያኗ መሪ ፅሁፎችና ትምህርቶች እና ከቅዱስ መጻህፍት ላይ የሚገኙትን መሰረቶች የያዘ እና ይህን መከተልም የሰማይ አባትን በረከት እና የልጁን መመሪያን የሚያመጣ ነው። በተጨማሪም፣ በጸሎት ከታሰበባቸው በኋላ በጥንቃቄ የተሰጋጁ የትምህርት መፅሐፎችም አሉ። ቤተሰቦችም የወንጌል መሰረት የሚማሩበት የቤተሰብ ምሽቶች አሏቸው። ብዙዎቻችሁም በሰምነሪ ክፍሎች ተሳታፊ የመሆን እድል አላችሁ።

ለቤተመቅደስ ጋብቻው፣ እና ለሚስዮንም ለመዘጋጀት ጀምሩ። ትክክለኛ የወንድና ሴት ቀጠሮም የመዘጋጀታችሁ ክፍል ነው። በወንድና ሴት ቀጠሮ ለመውጣት በሚቻልበት ባህልም፣ 16 አመታችሁ እስከሚሆን ድረስ አታድርጉ። ሁሉም ወጣቶች የወንድና ሴት ቀጠሮ መውጣታቸው አስፈላጊም አይደለም ወይም አይፈልጉም። እንደዚህ ቀጠሮ ሲኖራችሁ ከሌሎች ቡድኖች ጋር አብራችሁ ሂዱ። ከምታወጧቸውም ጋር ቤተሰቦቻችሁ እንዲተዋወቁ አድርጉ። በወንድና ሴት ቀጠሮ መውጣት ለጋብቻ መዘጋጂያ ስለሆነ፣ ከፍተኛ መሰረታዊ መመሪያ ካላቸው ጋር ብቻ ውጡ።

ጥሩ ነገሮች በሚገኙበት ቦታ፣ ፈተና በማያጋጥማችሁ በታ በመሄድ ተጠንቀቁ።

ጥበባዊ አባት ለልጁ እንዳለው፣ “መገኘት በማይገባህ ቦታ እራስህን ካገኘህ፣ ውጣ።”

የጌታ አገልጋዮች ለሰማይ አባታችን እና ለእራሳችን ክብር ለማሳየት ትክክለኛ ልብሶችን እንድንለብስ ሁልጊዜም ይመክሩናል። አለባበሳችሁ ለሌሎች ስለእናንተ መልእክት ይሰጣል እና እናንተና ሌሎች በምታደርሁት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በእናንተ እና በአካባቢያሁ ባሉት ጥሩ የሆነውን በሚያሳይ አለባበስ ልበሱ።፡ በአለባበስ እና በመልካችሁም በጣም ልዩ የሆኑትን፣ እንዲሁም ንቅሳትን፣ አስወግዱ።

ሁሉም ጥሩ ጓደኞች ያስፈልጋቸዋል። ጓደኞቻችሁ አስተሳሰባችሁን እና ጸባያችሁን ልክ እናንተ እነርሱ ላይ እንድሚኖራችሁ ተፅዕኖ አላቸው።ከጓደኞች ጋር አንድ አይነት ስነምግባር ሲኖራችሁ፣ እርስ በራስ ትጠናከራላችሁም ትበረታታላችሁም። ሁሉንም በደግነት እና በክብር ተመልከቱ። ብዙ አባል ያልሆኑ ወደ ቤተክርስትያኗ የመጡት በቤተክርስትያን ተሳታፊ ለማድረግ በሞከሩ ጓደኞች በኩል ነው።

ሁልጊዜም የሚደጋገመው “ታማኝነት ከሁሉም በላይ ጥሩ የሆነ መመሪያ ነው” የሚባለው አባባል እውነት ነው።፡ የኋለኛ ቀን ቅዱሳን ወጣት ሰው እንደሚያስተምረው እና እንደሚያምነው ይኖራል።፡ ከሌሎች ጋር ታማኝ ነው። በእራሱም ታማኝ ነው። ከእግዚአብሔር ጋርም ታማኝ ነው። በጸባይም በልምድም ታማኝ ነው። አስቸጋሪ ውሳኔ መደረግ በሚገባበት ጊዜም እራሱን “ሌሎች ምን ብለው ያስባሉ?” በማለት ሳይሆን “ስለእራሴ ምን አስባለሁ?” በማለት ይጠይቃል።

ለአንዳንዶች የግል መሰረታዊ መመሪያ እና ታማኝነትን የመስበር ፈተና ይመጣባቸዋል። በዩንቨርስቲ የንግድ ህግ ትምህርት በምማርበት ክፍል ውስጥ ለክፍል መወያየት የማይዘጋጅ አንድ ተማሪ ነበር። “የመጨረሻውን ፈተና እንዴት ነ የሚያልፈው?” ብዩ አስብ ነበር።

በክረምት ቀን ወደነበረን የመጨረሻው ፈተና ነጠላ ጫማ አድርጎ ሲመጣ መልሴን አገኘሁ። ተደንግጬ ክፍል ሲጀመር እርሱን እመለከት ነበር። መጽሀፎቹ በሙሉ በክፍሉ መሬት ላይ ተቀምጠው ነበር። ነጠላ ጫማውን አወለቀ፤ ከዛም ባሰለጠናቸው እና ባዝሊን በቀባቸው የእግር ጣቶቹ በመሬት ላይ ያስቀመጠውን መፅሀፍ ቀስ ብሎ ከፈተ። በዚህም ለፈተና ጥያቄዎ መልስን ለመመልከት ቻለ።

ከክፍል ታላቅ የሆነ ውጤታ አገኘ። ነገር ግን መልስ የሚሰጥበት ቀን መጣ። ለአጠቃላይ ፈተናው ሲዘጋጅ፣ አስተማሪው እንዲህ አለ፤ "በዚህ አመት ባህልን ቀይሬ የተጻፈ ፈተና ሳይሆን የቃል መልስ ፈተና አደርጋለሁ።" በእግር ጣት የተሰለጠነው ሰውም እግሩን በአፉ ውስጥ አገኛት እና ፈተናውን ወደቀ።

የምትናገሩት እና የምትመርጡት ቃላት ማን እንደሆናችሁ ለማሳየት እንደምትመርጡ ያሳያል። በአካባቢያችሁ ያሉትን የሚገነቡ እና ከፍ የሚያደርጉ ቋንቋዎችን ተጠቀሙ። ስድበት እና ቆሻሻ ንግግር እና ትክክል ያልሆነ ቀልድ ጌታን የሚያስከፉ ናቸው። የእግዚአብሔርን ወይም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም አትስደቡ። ጌታም "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ" ብሏል።

የሰማይ አባታችን "ምግባረ ጥሩ፣ የሚያስደስት፣ ወይም ጥሩ ሀተታ ወይም ምስጋና የሚገባው ምንም ነገር ካለ" እንድንፈልጋቸው መክሮናል። የምትሰሙት፣ የምታነቡት፣ ወይም የምትመለከቱት ተፅዕኖ ይኖሩባችኋል።

የወሲብ ነገሮችን የሚያሳዩት ሱስ የሚሰጡ እና አደገኛዎች ናቸው። እነዚህን ነገሮችን ለመመርመር መመልከት የሚቀጣጠራ ጸባይ ሊፈጥር እና ወደሚከፉ ነገሮች እና ወደ ወሲባዊ ኀጥያት የሚመራ ነው። የወሲብ ነገሮችን የሚያሳዩትን በማንኛውም መንገር አስወግዱ።

የሰማይ አባታችሁን መመሪያ መሰረት ጋር የማይስማማውን ከሚያሳዩ ሙቪ ለመውጣት፣ ቲቪን ለማጥፋት፣ ወይም የሬዲዮ መተላለፊያ ለመቀየር አትፍሩ። በአጭርም፣ ስለሙቪ፣ መጽሀፍ፣ ወይም ሌላ የምንጫወትባቸው ነገሮች ትክክል እንዳልሆኑ ምንም ጥያቄ ካላችሁ፣ አትዩት፣ አታንቡት፣ አትካፈሉበት።

ጳውሎስ እንዳወጀው፣ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? … የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።" ወንድሞች ቤተመቅደሳችንን የማፅዳት እና ንጹህ የማድረግ ሀላፊነት የእኛ ነው።

አደንዛዥ እጽ፣ መድሀኒትን ትክክል ባልሆነ መንገድ መጠቀም፣ መጠጥ፣ ቡና፣ ሻይ፣ እና የተባኮ ነገሮች ሰውነታችንን፣ አዕምሮአችንን፣ እና የመንፈስ ደህንነታችንን ያጠፋሉ። ማንኛውም አይነት መጠጥ ለመንፈሳችሁ እና ለሰውነታችሁ መጥፎ ናቸው። ተባኮ ባሪያ ያደርጋችኋል፣ ሳምባችሁን ያደክማል፣ እና ህይወታችሁንም ያሳጥራል።

ሙዚቃ ወደ ሰማይ አባታችሁ እንድትቀርቡ ያደርጋችኋል። ይህም ለማስተማር፣ ለማነፅ፣ ለማነሳሳት፣ እና አንድ ለማድረግ ለመጠቀም ይቻላል። ነገር ግን ሙዚቃም የመንፈሳዊ ስሜታችሁን ሊያደነድንም ይችላል። አዕምሮአችሁን ብቁ ባልሆኑ ሙዚቃዎች ለመሙላት አይገባችሁም።

የግብረ ስጋ ግንኙነት የተቀደሰ ስለሆነ፣ ጌታ ከጋብቻ በፊት እራስን እንድንቆጣጠርና ንጹህ እንድንሆን፣

እና ከጋብቻም በኋላ ታማኝ እንድንሆን ይጠብቅብናል። በቀጠሮ ስንወጣ፣ አብራችሁ የምትወጡትን አክብሩ እና እነርሱም እንዲያከብሯችሁ ጠብቁ። መተላለፍን እምባዎች መከተላቸው አይቀርምና።

የቤተክርስትያኗ ዘጠነኛ ፕሬዘደንት፣ ፕሬዘደንት ዴቪድ ኦ መኬይ እንዲህ መክረዋል፣ "ንጹህ ሀሳብ እንድታስቡ እለምናችኋለሁ። ስራችንን ለመቆጣጠር ከፈለግን፣ የምናስበውን መቆጣጠር አልብን።" ወንድሞች፣ አዕምሮአችሁን በቱ ሀሳባት ሙሉ፣ እና ስራዎቻችሁም ትክክል ይሆናሉ። ቴንሰን በጋለሀድ "ልቤ ንጹህ ስለሆነ ጥንካሬዬ እንደ አስር ሰው ጥንካሬ ነው" እንዳለው እናንተም በሉ።

ከትንሽ ጊዜ በፊት፣ ስለወጣቶች ጾታዊነት ሲናገር ህብረተሰቦች የተደበላለቀ መልእክት እንደሚልኩላቸው አሳይቷል፤ ማስታወቂያዎች እና መተላለፊያዎች "የወሲባዊ ግንኙነቶች ተቀባይ እና የሚጠበቁ ናቸው" የሚል መልእክት ይሰጣሉ። እነዚህም የሚያውቁት ሰዎችን ማስጠንቀቂያ እና የወላጆችን ልመና የሚያጠፉም ናቸው። በእነዚይ የመተላለፊያ መልእክቶች መካከል ግልፅ በሆነ ቋንቋ ጌታ "ንጹህ ሁኑ" ብሎ አውጆልናል።

ፈተና ሲመጣ፣ የሐዋሪያው ጳውሎስ ምክርን አስታውሱ፣ "ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።"

እንደቤተክርስትያኗ አባላት ስትረጋገጡ ለመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነት መብት ተቀብላችኋል። ጥሩ ምርጫ እንድታደርጉ ይረዳችኋል። ስፍተፈኑ፣ ብቸኝነት መሰማት አይገባችሁም። ጸሎት የመንፈስ ሀይል መግቢያ እንደሆነም አስታውሱ።

ማንም በጉዞው ቢሰናቀል፣ መመለሻ መንገድ አል። ይህም ንስሀ መግባት ነው። ያን የተባረከ ስጦታ አዳኛችን ሰጥቶናል። መንገዱ አስቸጋሪ ነው፣ የተስፋ ቃሉ ግን እውነት ነው፤ "ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች።"

የዘለአለም ህይወታችሁን አደጋ ላይ አትጣሉ። ኀጥያት ከሰራችሁ፣ ወዲያው መመለስ ከጀመራችሁ፣ ወዲያው በምህረት ታምራት የምትመጣውን ሰላ እና ደስታ ለማግኘት ትችላላችሁ። ደስታ የሚመጣው ጌታ እንድትኖሩ በሚፈልገው መንገድ በመኖር እና እግዚአብሔርን እና ሌሎችን በማገልገል ነው።

መንፈሳዊ ጥንካሬ የሚመጣው በራስ በማያስብ አገልግሎት በኩል ነው። ከብዙ አመቶች በፊት የካሊፎርንያ ሚስዮን ይባል በነበረው ቦታ ለመጎብኘት ሄጄ፣ ከጆርጂያ የመጣ ወጣት ሚስዮንን አነጋገርኩኝ። እርሱንም "ወደቤትህ በየሳምንት ደብዳቤ ትልካለህ?" አልኩት።

እርሱም "አዎን፣ ወንድም ሞንሰን" አለኝ።

ከዛም “ከቤትስ የሚመጣውን ደብዳቤ ትደሰትበታለህ?” አልኩት።

መልስ ግን አልሰጠኝም። ከጊዜ በኋላ “ከቤትህ ደብዳቤ ከደረሰህ ስንት ጊዜ ነው?” ብዬ ጠየቅኩት።

ድምጹም እየተንቀጠቀጠ፣ “ከቤት ደብዳቤ ደርሶኝ አላቅም። አባቴ ዲያቆን ነው፣ እና እናቴም የቤተክርስትያኗ አባል አይደለችም። እንዳልመጣ ለምነውኝ ነበር። ወደ ሚስዮን ከሄድኩኝ እንደማይጽፉልኝም ነግረውኝ ነበር። ምን ካድርግ?” አለኝ።

ለሰማይ አባቴ “አንተን ለማገልገል ሁሉንም መስዋእት ላደረገው ወጣት አገልጋይህም ምን ልበለው?” ብዬ ጸጥተኛ ሰሎት አደረኩኝ። ከዛም መነሳሻ መጣልኝ። እንዲህም አልኩት። “ካህን፣ በሚስዮንህ በየሳምንቱ ለእናትህ እና ለአባትህ ደብዳቤ ላክ። ምን እንደምታደርግ ንገራቸው። እንዴት እንደምትወዳቸውም ንገራቸው፣ ከዛም ምስክርህንም ስጣቸው።”

“ከዛም ይፅፉልኛል? ብሎ ጠየቀ።

እኔም “ከዛም ይፅሁልሀል” ብዬ መለስኩኝ።

ተለያየን፣ እና ወደሌላ ቦታ ሄድኩኝ። ከብዙ ወሮች በኋላ፣ በደቡብ ካሊፎርኒያ የስቴክ ጉባኤን እየተሳተፍኩበት እያለሁ አንድ ወጣት ሚስዮን ወደ እኔ መጣ እና “ወንድም ሞንሰን፣ ታስታውሱኛል? (ይህ ሁልጊዜ ይደርስብኛል) እኔ ከእናቱ ወይም ከአባቱ ለዘጠኝ ወር ደብዳቤ ያልደረሰው ልጅ ነኝ። እርሶም ‘ካህን በየሳምንት ወደቤትህ ደብዳቤ ላክ እና ወላጆችህ ይፅፉልሀል” ብለውኝ ነበር’” አለኝ። ከዛም “ይህን ቃል ኪዳን ያስታውሳሉ ካህን ሞንሰን?” አለኝ።”

አስታውሼ ነበር። “ከወላጆችህ ሰማህ?” ብዬ ጠየኩት።

ከኪሱ ብዙ ደብዳቤዎች አወጣ እና ከመካከላቸውም አንዱን አወጣ እና አለ፤ “ከወላጆቼ ሰምቼአለሁ! እናቴ የላከችልኝን ደድባቤ ስሙት፤ “ልጄ፣ ደብዳቤህን በጣም እንደሰትባቸዋለን። በአንተ በሚስዮናችንም ኩራት ይሰማናል። አባትሽ ወደቄስነት ተሾመ። እኔን ለመጥመቅ እየተዘጋጀ ነው። ከሚስዮኖች ጋር እየተገናኘሁ ነኝ፤ እና ከአንድ አመት በኋላ በሚስዮን አገልግሎትህ ቦታ በካልፎርኒያ በመምጣት ከአንተ ጋር በቤተመቅደስ ውስጥ ገብተን የዘለአለም ቤተሰብ ለመሆን እንፈልጋለን።’” ይህም ሚስዮን እንዲህ ጠየቀኝ፣ “ወንድም ሞንሰን፣ የሰማይ አባት ሁልጊዜም ጸሎትን ይመልሳል እና የሐዋሪያትን ቃል ኪዳን ያሚላል?”

እንዲህም መለስኩት፣ “ሰው እንዳለህ አይነት እምነት ሲያሳዩ፣ የሰማይ አባታችን እንደዚህ አይነት ጸሎትን ይሰማል እና በራሱም መንገድ ይመልሳል።”

ንጹህ እጅ እና ንጹህ ልብ፣ እና ፈቃደኛ አዕምሮ ሰማይን ነክቷል። ከሰማይ የተላከ በረከት የትሁት ሚስዮን ልብ ጸሎትን መልሷል።

ወንድሞች፣ ይህም እናንተ እንደዚህ እንድትኖሩና ሰማይም እንዲነካችሁ እና እንደዚህም እንድትባረኩ ጸሎቴ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።